# ጅቡ ሰውን በላው!

የዘመኑ ጅብስ ባህሉን ቀይሯል፣
ኑሮው በከተማ ቀለቡ ሰው ሆኗል።

አንድ ላይ ከትሞ መመከት ቢሳነው፣
እየነጣጠለ ጅቡ ሰውን በላው።

ሁሉም በየ ጎጡ ዘሩን ሲቆረጥም፣
ጅብ ሲዋጅ አደረ በስጋና በደም።

ሰውም አረመኔ ጭራሽ ጨካኝ ሆነ፣
የወገኑን እግር ጅብ ውጦት እያየ፣
አቀርቅሮ ያልፋል አይኑ አይቶ እንዳላዬ።

ምን ጉድ ነው?

የሰውን ልጅ እግር ቀኑ ቢያዳልጠው፣
ሐሞት የሌለው ጅብ በጊዜ የመጣው፣
በአቀንጣጤ ጥርሱ ይዞ ቆረጠመው።

ከጦቢያ ልጅ መንፈስ ከልቡም መሐከል፣
ፍርሃትና ትዕግስት ድንበራቸው ጠፍቷል፣
ግራ እግርህ ተበላ መላ ፍጠር ሲባል፣
ቀኜን እንዳይደግመኝ ዝም በሉ ይላል!

ሰው መተጋገዝ መረዳዳት ሲተው፣
ውሻን ጉርሻ አጉርሶ ጮሆ እንዳያሳጣው፣
እየነጣጠለ ጅቡ ሰውን ፈጀው፣

ተባረክ ያላለው ያልተመረቀ እገር፣
ጅብ ጥርሱን ተክሎበት ሲደማ ሲቆስል፣
ሲታከከው ያድራል ግራ ቀኙን ሊጥል ።

ቅጣትና እርግማን ወይንስ መተት ነው!
ድምጽ የሚፈራ ጅብ ዘንችሮ ሲበላው፣
ሰው ሰብሰብ ብሎ መጮህም ያቃተው?

ክፉ ቀን መጣና ጅቡ ሰውን በላው፣
ጭንቅላቱን ቀላ ልሳኑንም ዘጋው፣
አገሩን ሰው-አልባ ወና ሊያድረገው ነው።

እግዚኦ!

እባክህ አምላኬ ሰውን አገናኘው፣
ክልልና ጎጡን ድንበሩን ደርምሰው፣
በታቦት በመስጊድ አብረህ አጸልየው፣
በሰበብ አስባቡ ተበታትኖ ቢያየው፣
እየነጣጠለ ጅቡ ሰውን በላው።

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ታህሳስ ሁለት ሺህ አንድ ዓ.ም.